# ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት ማደግ

**ታሪኮች፡-**

1. ያዕቆብ---------------------------------------------------ዘፍ፡27፡1-37
2. የያዕቆብ መሰላል----------------------------------------ዘፍ፡28፡10-12
3. እግዚአብሔር የያዕቆብን ስም ቀየረው __________ዘፍ፡32፡1-30
4. ታዳጊዋ ቤተክርስቲያን ______________________የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን
5. የዳንኤል መንፈሳዊ ሕይወት እድገት ___________ዳን፡1
6. ራስን የመስጠት ፀሎት
7. ስለ ገንዘብ፡ ባለጠጋው ገዥ ____________________ማቴ፡19፡16-26
8. ገንዘብ ___________________________________ማቴ፡25፡14-30
9. ገንዘብና ገንዘብን መውደድ _______________________ሉቃ፡12፡13-34
10. ስግብግብነት፡ ንጉሡ አካብ ___________________1ነገ፡21፡1-25
11. ርኩሰት፡ ዮሴፍ ________________ዘፍ፡39
12. ዝሙት፡ ዳዊት __________________2ሳሙ፡11፡1-5 እና 2ሳሙ፡12፡7-14
13. ርኩሰት፡ _______________________ምሳ፡7፡1-27
14. ስለ ተቃራኒ ጾታ__________________1ቆሮ፡6፡9-20
15. ትዕቢት_________________________2ዜና፡26፡3-5፣ቁ.16-20
16. ትዕቢት ________________________ሉቃ፡18፡9-14
17. ሃይል፡ ያዕቆብና ዮሐንስ_____________ማቴ፡20፡17-28
18. ቁጣ፡ ቃየል______________________ዘፍ፡4፡1-16
19. ቁጣና ምቀኝነት፡ ሳኦል______________1ሳሙ፡18፡5-17
20. ቁጣ፡ ዳዊት______________________1ሳሙ፡24፡1-22
21. ቁጣ፡ ዮናስ______________________ት/ዮና፡4
22. መራራነት_______________________ኤፌ፡4፡31-32
23. ስግብግብነት፡ ኤሳው________________ዘፍ፡25፡29-34
24. ስንፍና _________________________ምሳሌ
25. ፍቅር አይሰርቅም_________________ኢያሱ፡7
26. ክለሳና ፀሎት

**ለመሪው፡-** እኛ ኢየሱስን እንድንመስል እግዚአብሔር ይፈልጋል፡፡ ይሁን እንጂ በመንፈሳዊ ሕይወት እንዳናድግ ከሐጢአት ጋር እንታገላለን፡፡ ይህ ተከታታይ ትምህርት እኛ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ኢየሱስን እየመሰልን እንድናድግ ይረዳናል፡፡ በእያንዳንዱ ሳምንት የቡድንህ አባላት ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት እንዲያድጉ አበረታታቸው፡፡ እርስ በርሳቸውም እንዲበረታቱ ንገራቸው፡፡ ከመሠረታዊ ጥያቄዎች አንዱ፡- ‹‹ በዚህ ሳምንት ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት እንዳድግ ይህ ታሪክ ምን ያስተምረኛል?›› የሚል ነው፡፡

**ለእያንዳንዱ የቡድን መሪ የሚጠቅም፡-** ከቡድንህ አባላት አንድ ሰው ለመምራት በሚመደብበት ጊዜ ከዚህ በታች ያሉትን ደረጃዎች እንዲጠቀም አበረታታው፡፡

**አንድን ታሪክ በጥሩ ሁኔታ ለመናገር የሚረዱ ደረጃዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡** የቡድኑ አባላት ታሪኩን የበለጠ ሲያውቁ ለማስታወስና ለማሰላሰል ይረዳቸዋል፡፡

- የቡድንህ አባላት ምን እንደሚማሩ፣ የተማሩትን ከሕይወታቸው ጋር እንደሚያዛምዱ፣ወይም ባለፈው ሳምንት ምን እንደተማሩ በመጠየቅ ጀምር፡፡ ከጥያቄዎቹ መካከል፡- ከታሪኩ ምን ያህል ተምረሃል? ባለፈው ሳምንት ታሪኩን ለሌላ ሰው ነግረሃል?
- ታሪኩ ሲነገር መጽሐፍ ቅዱስ መዘጋት አለበት፡፡ የታሪኩን ዋና ሀሳብ ተናገር እንጂ አንድ በአንድ ለመሸምደድ አትሞክር፡፡ ዋና ነጥቦችን ጠቅለል አድርገህ ለመናገር ሞክር፡፡
- ታሪኩን ሁለት ጊዜ ተናገር፡፡
- ከዚያም በኋላ እያንዳንዱ የቡድኑ አባላት ታሪኩን እንዲናገሩ አድርግ፡፡ አንዱ ሲናገር ቢቸገር ሌላው መርዳት ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ በቡድኑ አባላት ውስጥ በራስ መተማመን ይፈጠራል፡፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ትችላለህ፡- በመጀመሪያ ምን ሆነ? በዚያ ሥፍራ ማን ነበር? እነርሱ ምን አደረጉ? ቀጥሎ ምን አደረጉ? ሌላው ሰው ምን አለ? ወይም ምን አደረገ?
- አሁን እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን ተራ በተራ እንዲናገር አድርግ፡፡ ምናልባት የቡድንህ አባላት በቁጥር ብዙ ከሆኑ ቡድኑን ለሁለት በመክፈል በአንድ ቡድን አራት ወይም አምስት ሰው ሆነው ታሪኩን እርስ በርስ እንዲናገሩ ማድረግ ትችላለህ፡፡
- አሁን ታሪኩን አንብብ፡፡ ታሪኩ ሲነገር የቀረ ዋና ሀሳብ ካለ በነጥቡ ውስጥ አካትት፡፡
- መሠረታዊ ጥያቄ፡- ‹‹የዚህ ታሪክ ዋና ሀሳብ ምንድነው?››
- አሁን የቡድኑ አባለት ታሪኩን ለ7 ወይም 8 ጊዜ ሰምተዋል፡፡ ይህንን ታሪክ በቤት ከጎረቤቶቻቸውና ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲለማመዱ አበረታታቸው፡፡ በሚቀጥለው ሳምንት ይህንን ታሪክ ለአንድ ሰው እንዲናገሩ ንገራቸው፡፡
- ጊዜ ካለ የውይይት ጥያቄዎችን መጀመር ትችላለህ፡፡
- በሚቀጥለው ሳምንት ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ሲመጡ ታሪኩን መናገር አለመናገራቸውን ጠይቅ፡፡ ታሪኩን ከተናገሩ በኋላ ምን እንደተደረገ ጠይቃቸው፡፡
- የውይይት ጥያቄዎች ታሪኩን የበለጠ ለመረዳት የሚረዱ ናቸው፡፡ በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ የራስህን ውይይት ጥያቄ ማዘጋጀት ትችላለህ፡፡ ነገር ግን ከዋናው ሀሳብ መውጣት የለብህም፡፡
- በሚቀጥለው ሳምንት ታሪኩን በቃል እንዲናገር ከቡድንህ አባላት አንዱን ወክል፡፡

## ትምህርት፡1- ያዕቆብ

**መግቢያውን አንብብ ወይም ተናገር፡-** እያንዳንዱ አማኝ በመንሳዊ ሕይወት ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት እንዲያድግ እግዚአብሔር ይፈልጋል፡፡ ያዕቆብ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡ እርሱ የይስሐቅ ልጅ ነበር፡፡ ወንድሙ ኤሳው የመጀመሪያ ልጅ ቢሆንም እናታቸው ርብቃ ያዕቆብ የኤሳውን በረከት እንዲወስድ ፈልጋ ነበር፡፡ ያዕቆብ የስሙ ትርጉም አታላይ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ እርሱ በመጀመሪያ አታላይ ነበር፡፡ ስለ ያዕቆብ ሦስት ታሪክ እንማራለን፡፡ ከዚያም ይህ በእግዚአብሔር የተመረጠ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ ያደረገውን ትጋት እንመለከታለን፡፡ በዘፍ፡ 27 ላይ ያለው የመጀመሪያው ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

ታሪኩን በቅደም ተከተል ለመረዳት እንዲረዱ በተሰጡ ደረጃዎች መሠረት የቡድንህ አባላት ታሪኩን እንዲናገሩ አድርግ፡፡ በዚህ ጊዜ የያዕቆብ መንፈሳዊ ሕይወት እድገት ምን ይመስል ነበር፡፡ ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት ማደግን በተመለከተ የራስህን ሕይወት እንዴት ትገልጻለህ? በመንፈሳዊ ሕይወትህ ሕፃን፣ጎልማሳ፣ወይስ አዋቂ ነህ? ለምን?

**(ሁለተኛ ሣምንት)** ታሪኩን እንደገና የቡድንህ አባላት እንዲናገሩ አድርግ፡፡ አሁን ታሪኩን አንብብና ወደ ውይይት ጥያቄዎች ግባ፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. ያዕቆብ በዚህ ታሪክ ውስጥ ምን ዓይነት ሰው ነው? መልስህን አብራራ፡፡
2. ርብቃ በዚህ ታሪክ ውስጥ የተጫወተችው ሚና ምንድነው? ያዕቆብ የእናቱን ሀሳብ መቃወም ይችል ነበር? በሕይወታችን ስለሚነሱ ተጽዕኖዎች የምንማረው ምንድነው?
3. ዘፍ፡25፡23-28 አንብብ፡፡ እግዚአብሔር ለርብቃ ታናሹ ልጅ ታላቁ ላይ አለቃ እንደሚሆን ተናግሯት እያለ ለምን ያዕቆብና እርሷ ይስሐቅን ማታለል አስፈለጋቸው? ይህ ስለ እምነት ምን ያስተምርሃል?
4. በዚህ ጊዜ ያዕቆብ በሕይወቱ ከእግዚአብሔር ጋር ስለነበረው ግንኙነት ተወያዩ፡፡
5. ዛሬ እግዚአብሔር የሚያስተምርህ ምንድነው? በሕይወትህ ዘመን ሌላውን ሰው ያታለልክበት ጊዜ አለ?
6. በሕይወታችን ላይ የሚመጡ አዎንታዊ ተጽዕኖዎች ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት ለምናደርገው እድገት እንዴት ይረዱናል? አሉታዊ ተጽዕኖዎችስ እንዴት ይጎዱናል?
7. አሁን አንድ ሰው የሚቀጥለውን ሳምንት ታሪክ እንዲናገር ወኪል፡፡

## ትምህርት፡2 የያዕቆብ መሰላል

**መግቢያውን አንብብ ወይም በቃል ተናገር:** ያዕቆብ አባቱንና ወንድሙን አታለለ፡፡ ምኞቱን ፈጸመ፡፡ ይህ በሕይወቱ ብዙ ዋጋ አስከፈለው፡፡ ወንድሙ ኤሳው ሊገድለው ስለ ፈለገ መሸሽ ነበረበት፡፡ በዘፍ፡28 ላይ ያለው ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

ታሪኩን በቅደም ተከተል ለመረዳት እንዲረዱ በተሰጡ ደረጃዎች መሠረት የቡድንህ አባላት ታሪኩን እንዲናገሩ አድርግ፡፡

የታሪኩ ዋና ሀሳብ ምንድነው? በዚህ ጊዜ የያዕቆብ መንፈሳዊ ሕይወት ምን ይመስል ነበር?

(**በሚቀጥለው ሳምንት**) ታሪኩን እንደገና የቡድንህ አባላት እንዲናገሩ አድርግ። አሁን ታሪኩን አንብብና ወደ ውይይት ጥያቄዎች ግባ።

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን?
2. ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጋር በነበረው ግንኙነት ለማደግ ስላሳየው ጥረት ምን እንማራለን? እርሱ ለማደግ ያደረገውን ጥረት ለሌሎች ለማሳየት ያደረገው ምን ነበር?
3. በሕይወታችን የሚደርስብን መከራ ወይም ስደት ወደ እግዚአብሔር ለመጠጋት እንዴት ይረዳናል?
4. ያዕቆብ በመንፈሳዊ ሕይወቱ የሚያድገው ለምንድነው?
5. በሕይወትህ ለውጥ እንዲመጣ እግዚአብሔር ከሕይወትህ ያንከባለለው ነገር አለ? ስለዚህ ጉዳይ ከቡድንህ አባላት ጋር ተወያይ።
6. ዛሬ እግዚአብሔር የሚያስተምርህ ምንድነው?

## ትምህርት፡3 እግዚአብሔር የያዕቆብን ስም ለወጠው

**መግቢያውን አንብብ ወይም በቃል ተናገር፦** የራሄል አባት ያዕቆብን አታለለው። ነገር ግን ያዕቆብ ራሄልን ለማግባት ስለፈለገ ሰባት ዓመታትን በአባቷ ቤት ማገልገል ነበረበት። ያዕቆብ ከራሄል፣ሊያ እና ከሴት አገልጋያቸው አሥራ ሁለት ልጆችን ወለደ። እግዚአብሔር ያዕቆብን በብዙ እንስሳት ባረከው። ያዕቆብ አሁን ወደ አገሩ ለመመለስ ወሰነ። ይሁን እንጂ የወንድሙ ኤሳው ፍርሃት ከውስጡ አልጠፋም ነበር። በዘፍ፡32 ላይ ያለው የያዕቆብ ታሪክ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል። የያዕቆብ ሕይወት እንዴት እንደተቀየረ አድምጥ።

**ታሪኩን በቅደም ተከተል ለመረዳት እንዲረዱ በተሰጡ ደረጃዎች መሠረት የቡድንህ አባላት ታሪኩን እንዲናገሩ አድርግ።**

የታሪኩ ዋና ሀሳብ ምንድነው? በዚህ ጊዜ የያዕቆብ መንፈሳዊ ሕይወት ምን ይመስል ነበር? አሁን ታሪኩን አንብብና እያንዳንዱ ሰው በዚህ ሳምንት ታሪኩን እንዲናገሩ አበረታታቸው።

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. ያዕቆብ ፍርሃት ሲይዘው ቶሎ ወደ ፀሎት ይሄዳል። ስለ ያዕቆብና ስለመንፈሳዊ እድገቱ ምን እንማራለን?
2. የያዕቆብን ፀሎት ተማር። ስለ ያዕቆብ ምን ትማራለህ? ስለ እምነቱስ ምን እንማራለን?
3. ያዕቆብ ከፀሎቱ በኂላ የሚያደርገው ነገር ምንድነው?
4. ያዕቆብ ቤተሰቦቹን ወደ ማዶ ካሻገረ በኂላ ብቻውን ለመሆን የፈለገው ለምድነው?
5. ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጋር ከነበረው ትግሉ የምንማረው ነገር ምንድነው?
6. እግዚአብሔር የያዕቆብን ስም የለወጠው ለምንድነው?
7. ያዕቆብ ንስሐ የገባውና ከእግዚአብሔር ጋር ጤናማ ግንኙነት ያደረገው መቼ ነው?

8. ያዕቆብ ከአታላይነት ሕይወቱ ተለውጦ በመንሳዊ ሕይወቱ ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት ለመድረስ ያሳየውን ሂደት ከልስ፡፡

## ትምህርት-4፡ መቀደስ

**የመሪው ማስታወሻ**፡- ዛሬ ክርስቲያን ያልሆኑ ሚስቶችን መፍታትና ልጆችን መተው እንደሌለብን እግዚአብሔር ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ 1ቆሮ፡7፡12-13 አንብብ፡፡ ይህ የዚህ ታሪክ መወያያ ርዕስ አይደለም፡፡ ስለዚህ ይህንን ርዕስ በሌላ ቀን እስክንወያይ የቡድንህ አባላት እንዲጠብቁ አበረታታቸው፡፡

**መግቢያውን አንብብ**፡- ከእሥራኤል ሕዝብ አብዛኞቹ ጣዓትን ስላመለኩ በባቢሎን አገር በባሪነት እንዲቆዩ እግዚአብሔር ፈረደባቸው፡፡ ሰባው ዓመት በባቢሎን በተፈጸመ ጊዜ ከእሥራኤል ሕዝብ ግማሹ ወደ እሥራኤል አገር ተመለሱ፡፡ የአይሁድ ሰዎች የፈረሰውን ከተማ እንደገና እንዲሠሩ እግዚአብሔር እርሱን የማያውቅ ንጉሥ አስነስቶ ተናገራቸው፡፡ ይህ ንጉሥ እዝራን ልኮ ሕዝቡ የፈረሰውን ቤተመቅደስ እንዲገነቡ ሕዝቡን እንዲያስተባብር አደረገ፡፡ ቁ.7፣9 እና 10 ላይ የእግዚአብሔር እጅ ከእዝራ ጋር ስለነበረ፣እርሱም የእግዚአብሔርን ሕግ ለመማር ስለወሰነና እሥራኤላዊያንን ማስተማርን ስለተለማመደ እዝራ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ፡፡ ነገር ግን እዝራ ወደዚያ ሥፍራ ሲደርስ እግዚአብሔርን የማይከተሉ ቀድሞ በሥፍራው ይኖሩ የነበሩ ሰዎችን አገኘ፡፡ ታሪኩ ከመጽሐፈ ዕዝራ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በመሪው መመሪያ ላይ የተገለጹትን ደረጃዎች በመጠቀም እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን እንዲናገር አድርግ፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. የዕዝራ ልብ ትኩረት ያደረገው ምን ላይ ነበር?
2. ወደ እሥራኤል ከተመለሰው ሕዝብ ዕዝራ ያገኘው ችግር ምንድነው?
3. ለችግሩ ዕዝራ የሰጠው ምላሽ ምንድነው? ዕዝ፡9፡3-4 ተመልከት፡፡
4. ዕዝራ በፀሎቱ ጊዜ የተናዘዘው ምን ነበር?
5. የእሥራኤል ሕዝብ ቀድሞ በዚያ ሥፍራ ከነበሩ አህዛብ ሴቶች ጋር እንዳይጋቡ እግዚአብሔር ለምን አዘዘ? ከእነዚህ ሴቶች ጋር ግንኙነት መፍጠር አደጋው ምንድነው?
6. ሕዝቡ ለዚህ የሰጡት ምላሽ ምንድነው? ዕዝ፡10፡1-4 ተመልከት፡፡
7. የመቀደስ ትርጉሙ፡- ለእግዚአብሔር አገልግሎት መለየት ወይም ራስን አሳልፎ መስጠት ማለት ነው፡፡ ይህ ከዚህ ታሪክ ጋር እንዴት ይገናኛል?
8. መቀደስ ከሐጢአት ልምምድ ተለይቶ በቅድስና ሕይወት መመላለስ ነው፡፡ ሕዝቡ ለመቀደስ ምን ያህል ዋጋ አስከፈላቸው?
9. 1ተሰ፡4፡3 አንብብ፡፡ ክርስቲያን እንደመሆናችን እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፈቃዱ ምንድነው?
10. 1ተሰ፡5፡23 አንብብ፡፡ መቀደስ ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ርኩሰት መለየት ብቻ ነው ወይስ ከዚያ ያለፈ ነው?

11.1ጴጥ፡1፡14-19 አንብቡና ተወያዩበት፡፡
12.ለመቀደስ ምን ያህል ዋጋ ያስከፍላል ትላለህ?
13.እኛ እንዴት መቀደስ እንችላለን? ዮሐ፡17፡17 አንብብ፡፡
14.ሁሉም አማኞች ጌታን እንደተቀበሉ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ተቀድሰዋል፤ ወይም ተለይተዋል፡፡ ይህ የመጀመሪያው ደረጃ ነው፡፡ የሚቀጥለው ደረጃ በቅድስና ሕይወት ዕለት ዕለት እየተለወጡ መሄድ ነው፡፡ ሦስተኛው ደረጃ የወደፊት ሕይወት ነው፡፡ የመጨረሻው የቅድስና ደረጃ ከሐጢአት ሙሉ በሙሉ የምንለይበትና የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጊዜ ነው፡፡ አሁን በሕይወትህ የዕዝራን አርአያ እንዴት መከተል እንችላለን?
15.በሚቀጥለው ትምህርት ላይ የሚመጡ ታሪኮች በእምነታችን ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት ማደግ እንድንችል ያበረታቱናል፡፡ ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት ማደግና ቅድስና እንዴት አብረው ይሄዳሉ?

## ትምህርት፡5 የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን

<u>መግቢያውን አንብብ ወይም በቃልህ ተናገር፡</u>- ቆሮንቶስ ማዕከላዊ ከተማና ብዙ ጣዖታት የነበሩባት ከተማ ነበረች፡፡ ግብረ ሰዶማዊነት ከጣዖት አምልኮ አንዱ ሲሆን በዚያች ከተማ እንደ ባሕል ይወሰድ ነበር፡፡ በዚህች ከተማ ሐዋሪያው ጳውሎስ ቤተክርስቲያንን መስርቶ አዲስ አማኞች ጌታን በመፍራት እንዲኖሩ እያስተማረ ለአንድ ዓመት ከመንፈቅ ያህል ቆየ፡፡ ከዚያም ሐዋሪያው ጳውሎስ ከከተማዋ ወጣ፡፡ ነገር ግን በኋላ በቤተክርስቲያን ውስጥ ችግሮች እንደተፈጠሩ ሰማ፡፡ ከዚህ በታች ያሉትን ጥቅሶች አንብብና ችግሮችን ጥቀስ፡፡

1ቆሮ፡1፡11-14 --------------------------- እና---------------------------
1ቆሮ፡5፡1-----------------------------------------------------------------
1ቆሮ፡5፡2-----------------------------------------------------------------
1ቆሮ፡5፡9-13-------------------------------------------------------------
1ቆሮ፡11፡17-21----------------------------------------------------------

### የውይይት ጥያቄዎች

1. የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወት እድገት የነበሩበትን ደረጃ ግለጽ፡፡
2. ሐዋሪያው ጳውሎስ በዚህች ቤተክርስቲያን ውስጥ የነበሩትን ምዕመናን ስለ መንፈሳዊ ሕይወት አስተምሯቸው እያለ እነርሱ በመንፈሳዊ ሕይወት እንዳያድጉ ያደረጋቸው ምንድነው? ይህ በአንተ ሕይወት እንዴት ይታያል?
3. እነዚህ ምዕመናን ከመንፈሳዊ ሕይወትና ከራሳቸው ባሕላዊ የአኗኗር ዘይቤ የትኛውን መከተል አለባቸው?
4. በቤተክርስቲያንህ ውስጥ ያሉ ምዕመናን በቅድስና እንዳያድጉ የሚያደርጉ መንገዶች ምንድናቸው? በሌላ አነጋገር በሕይወትህ ወይም በቤተክርስቲያንህ ውስጥ ምዕመናን የሚታገሉት ከምን ዓይነት ሐጢአት ጋር ነው? ቅድስና ማለት ምዕመናን በሕይወታቸው ተለውጠው ከዓለማዊ ሀሳብ ተለይተው መኖር ማለት ነው፡፡
5. ለእነዚህ ችግሮች መፍትሔው ምንድነው? 1ቆሮ፡ 6፡19-20 እና 1ቆሮ፡10፡12 እና ቁ.13 አንብብ፡፡

6. በተጨማርም የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን የፀጋ ስጦታዎች አጠቃቀም ማለትም በልሳን መናገርና፣ትንቢት መናገር ችግሮች ነበሩባት፡፡ አንዳንዶቹ በትዕቢት ተሞልተው እነዚህን የፀጋ ስጦታዎች ስለሚጠቀሙ ሌሎች በአገልግሎታቸው አይታነጹም ነበር፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ በምዕ፡13 ላይ እጅግ በጣም የተሻለ መንገድ ያሳያቸዋል፡፡ ይህንን ክፍል አንብብና ፍቅር እንዴት ለእነዚህ ከላይ ለዘረዘርናቸው ችግሮች መፍተሔ እንደሚሆን ተወያይ፡፡
7. ዕብ፡5፡12-14 አንብብ፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወት ያላደጉ ሰዎች ምን ማድረግ ያስፈልጋቸዋል? ክፉውንና ደጉን እንዴት ማወቅ ይችላሉ?
8. በሕይወታችን ያለውን ሐጢአት ማየት እንድንችልና ንስሐ እንድንገባ በአንድነት ፀልዩ፡፡

## <u>ትምህርት-6፡ ዳንኤል</u>

***<u>መግቢያውን አንብብ ወይም በቃልህ ተናገር፡-</u>*** ዳንኤል ወደ ባቢሎን አገር በባርነት ሲወሰድ ወጣት ነበር፡፡ ለአዳዲስ ጌቶች መገዛትና በማያውቀው ባሕል ውስጥ መኖር ነበረበት፡፡ ታዲያ ዳንኤል በዚህ እንግዳ አገር ለአምላኩ ለመኖር መወሰን ነበረበት፡፡ ይህንን እውነተኛ ታሪክ ስማና በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ ይህንን ቁልፍ ትምህርት ለሕይወትህ መማር ትችላለህ፡፡

ታሪኩን ለመናገር በተሰጡ ደረጃዎች በመመርኮዝ እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን እንዲናገር አድርግ፡፡

***<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>***

1. ዳንኤልን የገጠመው ፈተና ምን ነበር?
2. ዳንኤል ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት ለማደግ እንዲረዳው ያደረገው ነገር ምንድነው?
3. ዳንኤል እግዚአብሔርን ስለታዘዘ እግዚአብሔር ለእርሱ የሰጠው ምንድነው?
4. ዳንኤል በእድሜው ሲገፋ እግዚአብሔር ራዕይን በመስጠት ባረከው፡፡ ዳንኤል ለብዙ ዘመናት ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነ፡፡ ት/ዳን፡12፡13 አንብብ፡፡ እግዚአብሔር ለዳንኤል የገባው ተስፋ ቃል ምንድነው?
5. በአእምሮአችን እግዚአብሔርን ለመከተል ስለ መወሰን ከዚህ ታሪክ ምን እንማራለን?
6. በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ምን ለማድረግ ትፈልጋለህ? ከአምስት ዓመታት በኂላስ? በሕይወትህ መጨረሻስ? ለምሳሌ፡- በሚቀጥለው ዓመት አንድ ቡድን አስተምራለሁ፤ደግሞም 25 የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን በቃል እናገራለሁ፡፡ ስለዚህ በሕይወትህ ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት ለማደግና ይህን ከላይ የተጠቀሰውን ግብ ለመድረስ ዛሬ የምትወስደው እርምጃ ምንድነው?
7. ልታደርጋቸው ያቀድካቸውን ነገሮች ዘርዝርና በመጽሐፍ ቅዱስህ ውስጥ አስቀምጥ፡፡ ከዚያም ከአንድ ዓመት በኂላ የዘርዘርካቸውን ነገሮች ከልስና እንዴት እንደምትተገብራቸው ገምግም፡፡

## ትምህርት-7፡ ገንዘብና ባለጠጋው ገዥ

***መግቢያውን አንብብ ወይም በቃል ተናገር***፡- ብዙ ሕዝብ ኢየሱስን ተከተሉት፡፡ እርሱም ብዙዎችን ከበሽታቸው ፈወሳቸው፤እንዲሁም ብዙ ሌሎች ተአምራትንም አደረገ፡፡ ይሁን እንጂ ኢየሱስን መከተል ብዙ ዋጋ እንደሚያስከፍል ካወቁ በኋላ ጥቂቶቹ ተስፋ ቆርጠው ወደኋላ ተመለሱ፡፡ ዛሬም ኢየሱስን ለመከተል ብዙ ዋጋ እየከፈልን ነው፡፡ ‹‹ዛሬ ኢየሱስን እንዳልከተልና ወደ እርሱ ፍጹም ሙላት እንዳላድግ የሚያደርገኝ ምንድነው?›› ብለን ራሳችንን ልንጠይቅ ይገባል፡፡ የዛሬው ታሪክ ትኩረት የሚያደርገው አንድ የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት የፈለገ ነገር ግን በሕይወቱ በዚህ ዓለም ነገር ስለተያዘ ሰው ነው፡፡ ይህ በማቴዎስ ወንጌል ያለው እውነተኛ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡
በመሪው መመሪያ ላይ ያሉትን ደረጃዎች በመጠቀም እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን በቃል እንዲናገር አድርግ፡፡ እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን በቃል ከተናገረ በኋላ አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጠይቅ፡- ‹‹የዚህ ታሪክ ዋና ሀሳብ ምንድነው?››

### የውይይት ጥያቄዎች

1. ቁ.20 ተመልከት፡፡ ሕግን ብቻ መጠበቅ ለዚህ ሰው በቂ ነበር?
2. ይህ ሰው ኢየሱስ የሚለውን ሁሉ ለማድረግ ፈቃደኛ ነበር? እርሱ ኢየሱስን እንዳይከተል የከለከለው ምን ነበር?
3. ቤተክርስቲያን ብትሄድና ትክክል የሆነውን ብታደርግ ይህ ብቻ ኢየሱስን ለመከተል በቂ ነው? ለምን?
4. ኢየሱስን የበለጠ እንዳትከተለው የዚህ ዓለም ነገር አንተን ወደኋላ የሚይዝባቸው መንገዶች ምንድናቸው?
5. ኢየሱስ እርሱን ለመከተል ለወሰኑት ዘላለማዊ ሽልማት እንደሚሰጥ የተስፋ ቃል ሰጥቷል፡፡ ይህ ተስፋ ቃል ከዓለማዊ ነገር ተለይተን እንድንኖር እንዴት ይረዳናል?
6. ዛሬ እግዚአብሔር አንተን የሚያስተምርህ ምንድነው?

## ትምህርት-8፡ የገንዘብ ምሳሌ

***መግቢያውን አንብብ ወይም በቃል ተናገር***፡- ገንዘብንና ሌሎች ንብረቶቻችንን እንዴት እንደምንጠቀም ለእኛ ሁሉን ነገር የሰጠውን እግዚአብሔር ይገደዋል፡፡ ደቀመዛሙርቱ ከዚህ ዓለም ነገር አይኖቻቸውን አንስተው በሰማዩ መንግስት ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ኢየሱስ አስተምሮአቸዋል፡፡ በተጨማሪም ኢየሱስ እርሱን ለሚከተሉት ደስታና ተድላ እንደሚሆን ተናግሯቸዋል፡፡ ይህንን ታሪክ ስማና በታሪኩ ውስጥ ላሉ ሰዎች ደስታን የሚሰጠው ምን እንደሆነ አስብ፡፡ ይህ ኢየሱስ ስለ ሰማዩ መንግስት ከተናገረው ምሳሌ አንዱ ነው፡፡ ይህም የሚገኘው በማቴዎስ ወንጌል ነው፡፡

በመሪው መመሪያ ላይ የተጠቀሱትን ደረጃዎች በመጠቀም እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን እንዲናገር አድርግ፡፡ ታሪኩን ተመልከት፡፡ ከዚህ ምሳሌ በፊት ኢየሱስ የተናገረው ምሳሌ ምን ነበር? በቁ.13 ላይ ያለው ማስጠንቀቂያ ምንድነው? የምሳሌውን ዋና ሀሳብ ለማወቅ ይህ እንዴት ሊረዳን ይችላል?

ታሪኩን አንብብና የቡድንህ አባላት በሚቀጥለው ሳምንት ታሪኩን እንዲናገሩ አበረታታቸው፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. ለእነዚህ ሁለቱ ሰዎች ደስታን የሰጠው ምን ነበር?
2. ለእኛ ያለንን ገንዘብና ሌሎች ንብረቶችን ኢየሱስ እንዴት እንድንጠቀማቸው ይፈልጋል?
3. በእግዚአብሔር መንግስት ስንኖር ነገሮችን ለግላችን መውሰድ ብቻ ሳይሆን የተቀበልነውን ነገር ለመንግስቱ ሥራ እንድናውል ነው፡፡ ጌታው በሦስተኛው ባሪያ ላይ የተቆጣው ለምንድነው?
4. ከገንዘብ ጋር በተያያዘ እኛን ታማኝ ያልሆኑ አገልጋዮች ሊያደርገን የሚችል ምንድነው?
5. አንዱ ባሪያ ተጨማሪ ገንዘብና ሃላፊነት ያገኘው እንዴት ነበር? እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት እንድናድግ ይህ ክፍል ምን ያስምረናል?
6. ይህንን ምሳሌ ከሕይወትህ ጋር እንዴት ልታዛምደው ትችላለህ?

**ማሳሰቢያ**፡- ከቻልክ ለቡድንህ አባላት ለእያንዳንዱ ከ10.00 ብር እስከ 50.00 ብር ድረስ ስጥ፡፡ ይህንን ገንዘብ በሚቀጥለው ሳምንት ለመንግስቱ ሥራ እንዲያውሉ ንገራቸው፡፡ በሚቀጥለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ሲመጡ የተቀበሉትን ገንዘብ ምን እንዳደረጉበትና ውጤቱ እንዴት እንደነበር ሪፖርት እንዲያደርጉ ንገራቸው፡፡

## ትምህርት-9፡ ገንዘብና ስስታምነት

**መግቢያውን አንብብ ወይም በቃል ተናገር**፡- ኢየሱስ ብዙ ተአምራትን ሲያደርግ ያየው ሕዝብ ሁሉ ይከተለው ነበር፡፡ ደቀመዛሙርቱ ከግብዝነት ሕይወት እንዲጠበቁ ጌታ ኢየሱስ አስጠንቅቋቸው ነበር፡፡ መብልና ደስታን ለማግኘት ብለህ ኢየሱስን አትከተለው፡፡ ምንም በስውር የሚያደርጉት ነገር እንደማይደበቅና ይልቁንም አስተሳሰባቸው፣ቃላቸውና ድርጊታቸው አንድ ቀን በብርሃን እንደሚገለጥ ኢየሱስ ነገራቸው፡፡ ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በመሪው መመሪያ ላይ የተገለጹትን ደረጃዎች በመጠቀም እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን በቃል እንዲናገር አድርግ፡፡

1. ይህ ምሳሌ ዛሬ ስለ ባለጠግነት ምን ያስተምርሃል?

**በምቀጥለው ሳምንት**፡- ታሪኩን እንደገና በቡድን ተናገሩና የውይይት ጥያቄዎችን ሥሩ፡፡

2. ሰውዬው ኢየሱስን የጠየቀው ምን ነበር? ኢየሱስ በቀጥታ ምላሽ ሰጠው? ኢየሱስ ለሰውየው የሰጠው ማስጠንቀቂያ ምን ነበር?
3. ስስታምነት ትርጉሙ፡- አንድ ሰው ሊኖረው ከሚገባው በላይ አንድ ነገር እንዲኖረው በምኞት መቃጠል ማለት ነው፡፡ ስስታምነት የሚለው፡- ገንዘብን፣ሥልጣንን፣ንብረትን ሊወክል ይችላል፡፡ ስስታምነት በአንድ አማኝ ሕይወት ግብዝነትን እንዴት መፍጠር እንደሚችል ተወያዩ፡፡
4. ስስታምነት በዚህ ሰውና በወንድሙ መካከል የነበረውን ግንኙነት እንዴት ጎዳው? ከኢየሱስ ጋር ያለውን ግንኙነትስ በምን መልኩ ጎዳው? ቁ.13 እና 14 ተመልከት፡፡
5. በእግዚአብሔር ዘንድ ባለጠጋ መሆን የምንችለው እንዴት ነው? ቁ.21 ተመልከት፡፡

6. አንድ አማኝ በገንዘቡና በንብረቱ ላይ ሊኖረው የሚገባው ትክክለኛው አመለካከት ምንድነው? 1ጢሞ፡6፡6-11 አንብቡና ተወያዩ፡፡
7. ዛሬ ኢየሱስ ሊያስተምርህ የፈለገው ምንድነው? ስስታምነትን ለመዋጋት ዛሬ ልንወስደው የምንችለው ተግባራዊ እርምጃ ምንድነው?

## ትምህርት-10፡ አክዓብና ስስታምነት

*<u>መግቢያውን አንብብ ወይም በቃል ተናገር</u>*፡- *ንጉሡ አክዓብ በብዙ መንገድ በእግዚአብሔር ላይ አመጸ፡፡ ከእግዚአብሔርና ከእግዚአብሔር ነቢያት እርምትን ከመቀበል ይልቅ በቁጣ ተዋጠ፡፡ እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ ሚስቱን ይሰማት ነበር፡፡ የዚህ ሰው ስስታምነት በመጽሐፈ ነገስት ላይ ቀርቧል፡፡*

*በመሪው መመሪያ ላይ ያሉትን ደረጃዎች በመጠቀም እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን እንዲናገር አድርግ፡፡*
*ይህ ታሪክ ስለምኞት ምን ያስተምርሃል አካብ በመንፈሳዊ ሕይወቱ አለማደግን እንዴት እንዳላሳየ ግለጽ፡፡*

*የውይይት ጥያቄዎች*፡
1. በባለፈው ትምህርት በተማርነው መሠረት የስስታምነት ትርጉሙ ምንድነው?
2. በቆላ፡3፡5 መሠረት ስስታምነት ጣዖት ተብሏል፡፡ በዚህ ታሪክ ውስጥ አክዓብ በልቡ ውስጥ የጣዖት አምልኮ እንዳለ እንዴት አሳየ?
3. የባልንጀራን ንብረት መመኘት እንዴት ወደ ከፋ ሐጢአት ሊመራ ይችላል?
4. የሐጢአትን ፈተና አክዓብ እንዲያስወግድ ሊረዳው የሚችለው ምንድነው?
5. እኛ በመጠን መኖር የምንችለው እንዴት ነው? ዕብ፡13፡5 አንብብ፡፡ እግዚአብሔር ለአንተ የገባው ተስፋ ቃል ምንድነው?
6. 1ጢሞ፡6፡6-11 አንብቡና እነዚህ ቁጥሮች ከዚህ ታሪክ ጋር እንዴት እንደሚገናኙ ተወያዩ፡፡
7. በባለፉት አራት ትምህርቶች ላይ ስለ ስስታምነት ተምረህ ነበር፡፡ ስስታምነት ራስን መውደድ ሲሆን ልብን ከእግዚአብሔር መንገድ ያስኮበልላል፡፡ ስስታምነት አደገኛ ችግር ስለሆነ ወደ ስርቆትና መስጠትን እምቢ ወደ ማለት ይመራል፡፡ ከስስታምነት ፈተና እንዴት መሸሽ እንደምትችል ከዚህ ታሪክ ምን ተምረሃል?

## ትምህርት-11፡ዝሙት፡ ዳዊት

*<u>መግቢያውን አንብብ ወይም በቃል ተናገር</u>*፡- *በዚህ ፈተና በሞላበት ዓለም ስንኖር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳይሆን የራሳችንን ፈቃድ እናደርጋለን፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወት እያደገ ያለ ክርስቲያን ትክክለኛ የሆነውን ነገር ለማድረግ መትጋት አለበት፡፡ የዝሙት ሐጢአት በጣም ትልቅ ችግር ሊሆን ይችላል፡፡ የዛሬው ታሪክ የሚያጠነጥነው በንጉሡ*

ዳዊት ሕይወት ላይ ነው፡፡ ታሪኩን አድምጥና ዳዊት እንዴት በሐጢአት ፈተና እንደወደቀ ተመልከት፡፡

በመሪው መመሪያ ላይ ያሉትን ደረጃዎች በመጠቀም እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን እንዲናገር አድርግ፡፡

1. ዳዊት በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያደገ ሰው መሆኑን እንድናስብ የሚያደርገን ምንድነው?
2. ዳዊት በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያደገ ሰው ነበር፡፡ ነገር ግን በሐጢአት ወድቋል፡፡ በታሪኩ መጀመሪያ ላይ እርሱ ያደረገው ምን ነበር? እንደ ንጉሥ በዚህ ጊዜ እርሱ ምን ማድረግ ነበረበት? ያ ምን ያስተምረናል?

<u>**በሚቀጥለው ሣምንት፡- የውይይት ጥያቄዎች**</u>

1. ታሪኩን እንደገና ከልስ፡፡
2. የዳዊት ሐጢአት ምን ነበር? ይህ የምስጢር ሐጢአት ነበር? እርሱ ሐጢአት እንደሰራ ያወቀው ማን ነበር? 2ሳሙ፡12፡9 አንብብ፡፡ በዚህ ክፍል ዳዊት ያቃለለው ምን ነበር?
3. ለዳዊት ሐጢአት እግዚአብሔር የሰጠው ምላሽ ምን ነበር? የሐጢአቱ ወጤት ምን ነበር?
4. ይህ የዳዊት ሐጢአት እርሱ ከሌሎች ማለትም ከጦር ሠራዊቶች፣ከሌሎች ሚስቶቹ፣ ከልጆቹ ወዘተ… ጋር የነበረውን ግንኙነት እንዴት አበላሸው?
5. አንዲት ሰውነቷን ጠበቅ አድርጎ የሚይዝና የሚገልጥ ልብስ የለበሰችን ቆንጆ ሴት ብታይ ምን ዓይነት አማራጭ ትወስዳለህ?
6. ፈተና በራሱ ሐጢአት አይደለም፤ነገር ግን ሐጢአትን ወደ ማድረግ የሚመራ ነው፡፡ ዳዊት ሐጢአትን ለመሥራት ያለፋቸውን የፈተና ደረጃዎች አስብ፡፡ እነዚህ ፈተናዎች ሲመጡበት እምቢ ማለት ይችል ነበር?
7. ኢየሱስ በልብ ውስጥ ሐጢአትን ለመሥራት መመኘት በራሱ ሐጢአት እንደሆነ ተናግሯል፡፡ የዝሙት ሐጢአት ፈተናን መቋቋም የምንችልባቸውን ተግባራዊ መንገዶችን ተወያዩ፡፡
8. ስለራስህ ግል ሕይወት አስብ፡፡ በስውር የምትሰራው ሐጢአት አለ? ይህ በእውነቱ ከማንም የተደበቀ ነው ማለት ትችላለህ? ዘኁል፡32፡23 ላይ፡- ‹‹እነሆ እግዚአብሔርን ትበድላላችሁ ሐጢአታችሁም እንዲያገኛችሁ እወቁ›› ይላል፡፡
9. እኛ ሐጢአትን ለመሥራት ስንፈተን የእግዚአብሔር ቃል ሊረዳን ይችላል፡፡ መዝ፡119፡9-11 ያለውን ክፍል በቃል አጥና፡፡

## <u>ትምህርት-12፡ ዮሴፍ፡ ርኩሰት</u>

<u>*መግቢያውን አንብብ*</u>፡- የዝሙት ፈተና ወደ ከፋ ሐጢአት እንደሚመራና ውጤቱም አስከፊ እንደሆነ ባለፈው ሳምንት ተምረን ነበር፡፡ ጋብቻ በክብር እንዲፈጸም የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ርኩሰት በማንኛውም ባሕል ትልቅ ችግር እየሆነ ነው፡፡ የዝሙት ርኩሰት ማንኛውም ከጋብቻ ውጪ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው፡፡ የዛሬው ታሪክ የሚያጠነጥነው አንድ የዝሙትን ፈተና እምቢ ባለው

ሰው ዙሪያ ነው። የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍን ጠልተውት ነበር። ከዚያም ለአንድ መንገደኛ ሸጡት። ያ መንገደኛ ደግሞ በተራው ዮሴፍን ለአንድ ግብፃዊ ለባርነት ሸጠው። ዛሬ ትኩረት የምናደርገው ዮሴፍ በግብጽ ምድር ያገኘውን ታላቅነት ሳይሆን በግብጽ ምድር በነበረበት ጊዜ የገጠመውን የዝሙት ፈተና ላይ ነው። ይህንን ታሪክ ስትሰማ ዮሴፍ እንዴት ወደዚህ ችግር እንደገባ አስብ። እርሱ ይህንን ችግር ማስወገድ ይችል ነበር? ታሪኩ ከዘፍጥረት መጽሐፍ እንደሚከተለው ቀርቧል።

በመሪው መመሪያ ላይ ያሉትን ደረጃዎች በመጠቀም እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን እንዲናገር አድርግ።
ስለ ዝሙት ፈተና ይህ ታሪክ ምን ያስተምርሃል? ዮሴፍ ይህንን የዝሙት ፈተና አሸንፎ ነበር?

የውይይት ጥያቄዎች

1. የጶጥፋራ ሚስት ለዮሴፍ የዝሙት ጥያቄ ከማቅረቧ በፊት ሕይወቱ ምን ይመስል ነበር?
2. ዮሴፍ የእግዚአብሔር ሰው ስለ መሆኑ የሚያሳይ ምን ማረጋገጫ አለ?
3. እርሱ ችግሩን ለማስወገድ ሊያደርገው የሚችለው ነገር ነበር?
4. ዮሴፍ ፈተናን ለመቋቋም ያደረገው ነገር ምን ነበር?
5. ዮሴፍ ከሴቲ ጋር ዝሙትን ላለመፈጸም የሰጠው ምክንያት ምን ነበር? የእግዚአብሔር መመሪያ ምንድነው?
6. የዳዊትን ሁኔታና የዮሴፍን ሁኔታ በማነጻጸር ተወያዩ። ከዚህ ምን ትማራለህ? ዳዊት በርሳቤን ካያት በኋላ በመጀመሪያ ያደረገው ነገር ምንድነው?
7. 1ተሰ፡ 4፡1-8 አንብብ። እግዚአብሔር ለክርስቲያኖች ስላለው በጎ ፈቃድ ከዚህ ምን ትማራለህ? አንተ ከመንፈሳዊ ሕይወት ውጭ ስትመላለስ የማንን ሀሳብ ነው የምትቃወመው?
8. አንድ ሰው በዝሙት መንፈስ ሲቃጠል ወይም በዝሙት ፈተና ውስጥ ሲገባ ምን ማድረግ እንዳለበት ከዚህ ምን ትማራለህ?

## <u>ትምህርት-13፡ ርኩሰት</u>

***<u>መግቢያውን አንብብ</u>***፡- ሰይጣን አታላይና የውሸት አባት ነው። ዳዊት ለእግዚአብሔር የልቡ ሰው ቢሆንም በሰይጣን ተታልሎ በእግዚአብሔር ላይ ማመጹን ተምረን ነበር። ሰይጣን በፊታችን ወይም በልባችን አንድን ነገር ቆንጆ አድርገን እንዲናይ ለማድረግ ጥረት ያደርጋል። የዳዊት ሐጢአት እርሱን ብዙ ዋጋ አስከፍሎታል። በእንደዚህ ዓይነት ሐጢአት ብዙ ጊዜ ወንዶች በቀላሉ ይፈተናሉ። እኛ ሐጢአት መሥራት እንደሌለብን የምሳሌ መጽሐፍ ያስተምረናል። ንጉሡ ሶሎሞን ለልጁ የሰጠውን ምክር በጥንቃቄ ከታሪኩ ተመልከት።

በመሪው መመሪያ ላይ ያሉትን ደረጃዎች በመጠቀም እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን እንዲናገር አድርግ።

**<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>**

1. ስለዚህች ርኩሰት ስለተለማመደች ሴት ምን ትማራለህ? እርሷ ሰውዬውን የተፈታተነችው እንዴት ነበር?
2. ስለ ወንዶች በተለይም ስለ ወጣት ወንዶች ምን ትማራለህ?
3. የዝሙት ሐጢአት ብትሠራ ውጤቱ ምን ይሆናል?
4. አንተ ባለህበት ማህበረሰብ ውስጥ እንደዚህች ዓይነት ሴት የት ትገኛለች?
5. ምሳሌ፡5፡1-14 አንብብ፡፡
6. ርኩሰትን ስለማስወገድ ምን ትማራለህ?
7. ክርስቲያን ሴቶች ባሎቻቸው በዝሙት ፈተና እንዳይወድቁ መርዳት ይችላሉን? ምን ማድረግ ይችላሉ?

## ትምህርት-14፡ ስለ ተቃራኒ ፆታ

***መግቢያ***፡- የዝሙት ሐጢአት በጣም አደገኛ ነው፡፡ ደግሞም በሰው ሕይወት ውስጥ ትልቁ ፈተና እርሱ ነው፡፡ በ1ቆሮንቶስ ላይ ዛሬ እግዚአብሔር ስለዚህ ሐጢአት የሚለውን እናጠናለን፡፡ ይህ ትምህርት ሁለት ሳምንት ላይበቃው ይችላል፡፡ ከተቃራኒ ፆታ ጋር በተያያዘ ከእግዚአብሔር ሰዎች የምክር አገልግሎትና የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅ ትችላላችሁ፡፡

**1ቆሮ፡6፡9-20 አንብብ፡፡**

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. መንግስተ ሰማያት ሊገቡ የማይችሉ ሐጢአተኞች የትኞቹ እንደሆኑ ዘርዝር፡፡ እነዚህ ሰዎች ሐጢአት መሥራትን የማያቆሙና ንስሐ የማይገቡ ሰዎች ናቸው፡፡
2. በቁ.9 ላይ እግዚአብሔር የሚያስጠነቅቀን ምንድነው? አንድ ሰው እኔ ክርስቲያን ነኝ ቢልም በእነዚህ ሐጢአቶች ሊፈተን የሚችለው እንዴት ነው?
3. በቁ.11 መሠረት በእውነተኛ አማኝ ሕይወት የሚሆነው ምንድነው?
4. ስለ ሰውነታችን የምንማረው ምንድነው?
5. በቁ.18 ላይ እግዚአብሔር የሚሰጠው ትዕዛዝ ምንድነው?
6. የዝሙት ሐጢአት ትርጉሞች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡-
   ***ዝሙት***፡- ይህ ከጋብቻ ውጭ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ ነው፡፡
   ***አመንዝራነት***፡- ከባለትዳሮች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ ነው፡፡
   ***ግብረ ሰዶማዊነት***፡- ከተመሳሳይ ፆታ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ ነው፡፡
   ***የንጽሕና ጉድለት***፡- በኮምፒዩተርና በመሰል ነገሮች ውስጥ የሚለቀቁትን ፎርኖግራፊዎችን መመልከትና በምኞት መቃጠል ነው፡፡
   ***ፎርኖግራፊ***፡- በፎቶና በቪድዮ የሚሠራጩትን ወሲብ ቀስቃሽ ፍልሞችን መመልከት ነው፡፡
   ***መመኘት***፡- በትዳር ካልተጣመርናቸው ሰዎች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለማድረግ በልባችን መመኘት ማለት ነው፡፡
7. ኤፌ፡5፡3-15 አንብብ፡፡
   ከዚህ ምን እንማራለን?
   እንዴት መኖር አለብን?
8. በፈተና ድልን ልናገኝ የምንችለው እንዴት ነው? ገላ፡5፡16-25

9. ዛሬ በአፍሪካ አዳዲስ ፈተናዎች እየመጡ ነው፡፡ ዓለም በውሸት የተሞላች ስለሆነ ውሸቷን እንድታምን ትመራሃለች፡፡ በዝሙት እንድትወድቅ ታታልላሃለች፡፡ ከዚህ በታች ስላሉ ችግሮች ተወያዩ፡፡

    1. ከምዕብራቡ ዓለም የሚመጡ ፍልሞች
    2. በኢንተርኔት የሚለቀቁ ፎርኖግራፊዎች
    3. አዲስ ከምዕራቡ ዓለም የመጡ የሴቶች ፋሽን ልብሶች
    4. ወደ ዮኒቨርሲቲ መግባትና አዲስ ነጻነትን መለማመድ
    5. በግል ቤት ውስጥ ሚስትህ ካልሆነች ሴት ወይም ባልሽ ካልሆነ ወንድ ጋር አብሮ መኖር

***<u>ማጠቃለያ</u>***፡- *ፆታን የፈጠረው እግዚአብሔር ነው፡፡ ለእኛ የሚበጀውን እርሱ ስለሚያውቅ እንዴት መኖር እንዳለብን ሕግን ሰጥቶናል፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ፍጹምና እንከን የሌለው ነው፡፡ (ሮሜ፡12፡2) ባለትዳሮች ትዳራቸው ዘለቄታ እንዲኖረው ሁለቱ በመካከላቸው ደስተኛ ኑሮ እንዲኖሩ የእግዚአብሔር ሃሳብ ነው፡፡ በዚህ ዙሪያ የበለጠ ምክር ካስፈለገህ የምክር አገልግሎት መጠየቁ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ብልህ ልትሆን ይገባሃል፡፡ በዚህ ዙሪያ ማንበብ ከፈለግህ በሴቶች ግርዛት ዙሪያ ሳንዲ ዊሊኮክስ (Sandy Willcox) በተባለች ሴት የተጻፈ መጽሐፍ በኤስ አይ ኤም (SIM) ድርጅት መጽሐፍት መደብር ስለሚገኝ ብታነብ ተጠቃሚ ትሆናለህ፡፡*

## <u>ትምህርት-15፡ ትዕቢት</u>

***<u>መግቢያውን አንብብ ወይም በቃል ተናገር</u>***፡- *ትዕቢት በአዳምና ሔዋን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የኖረ ሐጢአት ነው፡፡ <u>ትዕቢት ከእግዚአብሔር ውጭ በራስ ላይ መደገፍ ነው</u>፡፡ ስኬታችን በራሳችን ሀይልና ችሎታ የመጣ ነገር አድርገን እናስባለን፡፡ ለእኛ የተሻለውን ነገር እኛ እናውቃለን ብለን እናስባለን፡፡ የዛሬው ታሪክ ከቆሮንቶስ መጽሐፍ ውስጥ ነው፡፡ ይህ የንጉሡ ኦዝያን ታሪክ ነው፡፡ እግዚአብሔር ስለረዳው በብዙ ሕዝቦች ዘንድ ይታወቅ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አይኑን ከእግዚአብሔር ላይ አነሳ፡፡ ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡*

*በመሪው መመሪያ ላይ ያሉትን ደረጃዎች በመጠቀም እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን እንዲናገር አድርግ፡፡*

***<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>:***

1. *ትዕቢት ምንድነው እንዴት ትገልጸዋለህ?*
2. *ኦዝያን የታበየው መቼ ነበር?*
3. *እርሱ የሠራው ስህተት ምን ነበር? ያ እንዴት ከትዕቢት ጋር ይገናኛል?*
4. *ኦዝያንን ለማረም ስለሞከሩ ካህናት ኦዝያን የነበረው አመለካከት ምን ነበር?*
5. *የኦዝያን ሐጢአት ውጤቱ ምን ነበር?*
6. *ስለ ሁለተኛው ትዕቢተኛ ንጉሥ በ2ዜና 32፡24-26 አንብብ፡፡ ስለ ትዕቢትና ንስሐ ስለመግባት ከዚህ ምን ትማራለህ?*

7. በሕይወታችን ስሳካልን የምንሰጠው ምላሽ ምንድነው?
8. ዛሬ እግዚአብሔር የሚያስተምርህ ምንድነው?

## <u>ትምህርት-16፡ ትዕቢት</u>

***<u>መግቢያውን አንብብ ወይም በቃል ተናገር</u>***፡- አብዛኛዎቻችን ከትዕቢት ጋር እንታገላለን፡፡ ትዕቢት በብዙ የሕይወታችን ክፍሎች ይታያል፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንዳንታበይ ኢየሱስ ማስጠንቀቂያ ስጥቶናል፡፡ ቃሉ በሉቃስ ወንጌል ይገኛል፡፡

በመሪው መመሪያ ላይ ያሉትን ደረጃዎችን በመጠቀም እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን እንዲናገር አድርግ፡፡

የውይይት ጥያቄዎች

1. ኢየሱስ ይህንን ታሪክ የተናገረው ለማን ነው?
2. በምሳሌው ላይ ስለሚገኙ እያንዳንዱ ሰዎች የምንማረው ምንድነው? አንዱ ከሌላው የሚለየው እንዴት ነው?
3. በእግዚአብሔር ፊት ፃድቅ ማነው? ለምን?
4. በመንፈሳዊ ሕይወት እኔ ከሌላው እሻላለሁ ብሎ የሚያስብ ሰው ራስ ወዳድ ጻድቅ ይባላል፡፡ ይህ ራስ ወዳድ ጻድቅ የመሆን ትዕቢት በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንዳናድግ እንዴት ይጎዳናል?
5. ከእነዚህ ሁለቱ ሰዎች በብዛት የትኛውን ትመስላለህ? በዚህ ሳምንት በሕይወትህ ለውጥ እንዲመጣ ምን ታደርጋለህ?

## <u>ትምህርት-17፡ ሃይል (ሥልጣን)፡ ያዕቆብና ዮሐንስ</u>

***<u>መግቢያውን አንብብ</u>***፡- በሕይወታችን ሃይለኛ ለመሆን እንድንመኝ ከሚያደርገን ትዕቢት ጋር እየታገልን ነው፡፡ 12ቱ ሐዋሪያትም ተመሳሳይ ችግር ነበረባቸው፡፡ ይህንን ታሪክ ከማቴዎስ ወንጌል ስትሰማ አንተ ባለህበት ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ መሪዎች ባሕሪ አስብ፡፡ የሚመሩትን ሕዝብ እንዴት ይመለከታሉ?

በመሪው መመሪያ ላይ ያሉትን ደረጃዎች በመጠቀም እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን እንዲናገር አድርግ፡፡

***<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>***

1. እናት ስለ ልጆቿ ደረጃ ኢየሱስን ከመጠየቋ በፊት የሆነው ነገር ምን ነበር? እነርሱ በእውነቱ ኢየሱስን ይሰሙት ነበር? ይህ ሰዎች ስልጣንን ቀድሞ ለመያዝ ስለሚያደርጉት ሽኩቻ ምን ይናገራል?
2. አንተስ ራስህን እንዴት ታያለህ? ስለ ራስህ ስልጣን እያሰብክ እግዚአብሔር የሚናገርህን እንዳትሰማ እምቢ ብለሃልን? ስለዚህ ጉዳይ ተወያዩ፡፡

3. ብዙ ሰዎች መሪዎች ለመሆን እንዲመኙ የሚያነሳሳቸው ምንድነው?
4. አንድ ሰው መሪ ለመሆን እንዴት እንደሚችል ኢየሱስ ያስተማረው ምንድነው?
5. አንድ ጥሩ መሪ ከሚመራቸው ሰዎች ጋር ያለው ግንኙነት እንዴት እንደሆነ ኢየሱስ ያስተማረው ምንድነው?
6. አንድ የክርስቲያን መሪ ጥሩ መለኪያዎች ምን እንደሆኑ ኢየሱስ የተናገረው ምን ነበር?
7. አንተ ያለህበት ባህል ይህንን ነገር ያስተምራል?
8. ኢየሱስ ለማገልገል መጣ የሚለው ምን ማለት ነው? ይህ በአኗኗርህና በአመራርህ ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ ምንድነው?
9. በሥራ ቦታ፣በቤት ወይም በቤተክርስቲያን ውስጥ በአንተ መሪነት ሥር ያለውን አንድ ሰው አስብ፡፡ በዚህ ሳምንት በአመራርህ ላይ እንዴት ለውጥ ማምጣት ትችላለህ?

## ትምህርት፡18፡ ቁጣ

**መግቢያ**፡- ማንኛውም ሰው አንዳንድ ጊዜ ይቆጣል፡፡ ኢየሱስ ራሱ ተቆጥቷል፤ነገር ግን ሐጢአት አልሠራም፡፡ (ዕብ፡4፡15) ፡፡ እኛ ሁላችንም የቁጣ ስሜታችንን መቆጣጠር ያቅተናል፡፡ ከዚህም የተነሳ ሐጢአት እንሠራለን፡፡ ጥቂቶቻችን የማይቆረጡ ችግሮች አሉብን፡፡ የቃየልና አቤል ታሪክ ከዚህ ጋር ይመሳሰላል፡፡ ነገር ግን ይህንን ታሪክ ስትሰማ ቁጣ የሚለውን ቃል ልብ በል፡፡ ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በመሪው መመሪያ ላይ ያሉትን ደረጃዎች በመጠቀም እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን እንዲናገር አድርግ፡፡

1. ቃየል የተቆጣው በማን ላይ ነው? በራሱ ላይ? በወንድሙ ላይ? ወይስ በእግዚአብሔር ላይ?
2. ቃየል የተቆጣው ለምንድነው?
3. ምቀኝነት ወደ ቁጣና ሐጢአት ሊመራ ይችላል፡፡ ይህ ታሪክ ይህንን እውነት እንዴት እንደሚያሳይ ተወያዩ፡፡
4. ቃየል ስለተቆጣ እግዚአብሔር ምን ዓይነት ትዕዛዝ ሰጠው?
5. ቃየል ትክክለኛ የሆነውን ነገር ማድረግ እንደነበረበት እግዚአብሔር ነገረው፡፡ እግዚአብሔር ከተናገረው በኋላ ቃየል ወዲያው ሊያደርጋቸው የሚችላቸው ነገሮች ምን ነበሩ?
6. እኛ ቁጣችንን እንድንቆጣጠር እግዚአብሔር ትዕዛዝ ሰጥቶናል፡፡ ራስን ስለመግዛት ከሚከተሉ ክፍሎች ምን ትማራለህ? (ገላ፡5፡22-23፤1ቆሮ፡9፡25-27፤2ጢሞ፡1፡7
7. አንድ ያስቆጣህ ሰው እያለ ያንን ቁጣ በሌላ ሰላማዊ ሰው ላይ ተወጥተህ ታውቃለህ? በልብህ ባልንጀራህን ገድለሃል ማለት ነው፡፡ በልባችን ስለምናደርገው ጥፋት ኢየሱስ አስጠንቅቆናል፡፡ (ማቴ፡5፡20-22)
8. ከቁጣ የተነሳ የጎዳኸው ሰው አለ? ከዚህ ሰው ጋር ጤናማ ግንኙነት እንዲኖርህ ዛሬ ምን ማድረግ አለብህ?
9. ዛሬ እግዚአብሔር የሚያስተምርህ ምንድነው?

10. ዛሬ ራሳችንን እንድንገዛ እግዚአብሔር እንዲረዳን ከእርሱ ምን እንጠብቃለን?

## ትምህርት 19፡ ቁጣና ምቀኝነት፡ ሳኦል

***መግቢያ***፡- እኛ ሁላችንም በተለያየ ጊዜ የቁጣ ስሜት ያድርብናል፡፡ ይሁን እንጂ ያ ስሜት ሐጢአት አይደለም፡፡ በኤፌ፡4፡26 ላይ፡- ‹‹ተቆጡ ሐጢአትንም አታድርጉ›› ይላል፡፡ ስለዚህ ቁጣን የምንገልጽበት አገላለጽ ወደ ሐጢአት ሊመራን ይችላል፡፡ ሰዎች ቁጣን በተለያዩ መንገዶች ይገልጻሉ፡፡ በ1ሳሙኤል መጽሐፍ ላይ ንጉሡ ሳኦል ቁጣውን እንዴት እንደሚገልጽ ከዚህ ታሪክ ስማ፡፡

በመሪው መመሪያ ላይ ያሉትን ደረጃዎች በመጠቀም እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን እንዲናገር አድርግ፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. ንጉሡ ቁጣውን እንዴት በዳዊት ላይ አሳየ?
2. ንጉሡ ሳኦል እንዲቆጣ ምክንያት የሆነው ምንድነው?
3. ***ምቀኝነት*** ማለት አንተ የምትፈልገው ነገር ለሌላው ሲኖር አለመደሰት ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ለሌላው ሲሳካለት እኛ ሳንደሰት ስንቀር ይህ ምቀኝነት ነው፡፡ ወይም በሌላው አለመሳካት እኛ ስንደሰት ማለት ነው፡፡ ምናልባት ስትቆጣ እንደ ሳኦል ጦር ላትወረውር ትችላለህ፡፡ ነገር ግን በአንተ ባሕል ምቀኝነት የሚገለጸው እንዴት ነው?
4. ከምቀኝነት የተነሳ አንድን ሰው ጠልተህ ወይም አጠገቡ እንኳን መቀመጥ አስጠልቶህ ያውቃል? ትዕቢት፣ቁጣና ምቀኝነት የተያያዙ ነገሮች ናቸው፡፡ ትዕቢት በራስህ ላይ ብቻ ትኩረት ማድረግ ነው፡፡ እግዚአብሔር ይቅር እንዲልህ ለምነው፡፡ ራስህን ብቻ ማየትን ትተህ እግዚአብሔርን እንድታይ እርሱ እንዲረዳህ ለምነው፡፡
5. ቁጣ እንዴት እንደሚገለጽ ከምሳ፡29፡11 እና ቁ.20 ምን ትማራለህ? ሰነፍ ሰው ቁጣውን ሁሉ ***ያወጣል***፤ጠቢብ ግን በውስጡ ***ያስቀረዋል***፡፡ በቃሉ የሚቸኩለውን ሰው ብታይ ከእርሱ ይልቅ ለሰነፍ ተስፋ አለው፡፡
6. ቁጣ የሚገለጽበት አንዱ መንገድ በቃልና በድርጊት ሃይለ ቃልን መጠቀም ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንድናደርግ ነው የሚያስተምረን? ምሳ፡16፡32፡ ትዕግሥተኛ ሰው ከኃያል ሰው ይሻላል፤በመንፈሱም ላይ የሚገዛ ከተማ ከሚወስድ ይበልጣል፡፡
7. የንጉሡ ሳኦል ልብ በክፋትና ዳዊትን ለመጉዳት ባለው ምኞት የተሞላ ነው፡፡ አመለካከታችን ቃላችንንና ተግባራችንን እንደሚቆጣጠር መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል፡፡ አመለካከታችንና ስሜታችንን መቆጣጠር ያስፈልገናል፤ምክንያቱም ወደ ሐጢአት የሚመራ አመለካከት ካለን በቀላሉ ወደ ሐጢአት እንገባለን፡፡ ምሳ፡4፡23 እና ማቴ፡15፡18 እና ቁ.19 አንብቡና ተወያዩ፡፡
8. በቁጣ ቃል ሌሎችን ትጎዳና በኋላ ለራስህ ጸጸት ይሆንብሃል፡፡ ሌሎችን በቁጣችን የጎዳን ከሆነ ምን ማድረግ አለብን?
9. የቁጣን ልምድ እንድናስወግድ እንዲረዱን ከዚህ በታች በተቀመጡ ሀሳቦች ላይ ውይይት አድርጉ፡፡
   ሀ. ሊያስቆጣህ የሚችለውን ሁኔታ መርምረው፤እንዲሁም አንድን ነገር ካልክ ውይም ካደረክ በኋላ ሊመጣ የሚችለውን ውጤት ከግንዛቤ አስገባ፡፡
   ለምሳሌ፡- ‹‹ የምናገረው ወይም የማደርገው ነገር ለሌሎች መልካም ይሆናል

ወይስ ግድ የለም ልቆጣና በኋላ ልጸጸት›› ማለት

ለ. እስከ 10 ወይም 20 ወይም 100 ድረስ ቁጠር፡፡

ሐ. ስትቆጣ ጥለህ ውጣና ለመዝናናት ሂድ ወይም ቁጭ በልና ያስቆጣህን ነገር አስብ፡፡

መ. ለትንሹ ልጄ፡- ‹‹በእህትህ ላይ ከተቆጣህና ልትመታት ብትፈልግ በፍጥነት ሩጥ ወይም ትራስህን ምታ›› እለዋለሁ፡፡

## <u>ትምህርት፡20፡ ቁጣ፡ ዳዊት</u>

***<u>መግቢያ</u>***፡- ንጉሡ ሳኦል በዳዊት ላይ ስለቀና እጅግ ተቆጣ፡፡ ዳዊትን ሊይዘውና ሊገድለው ፈልጎ ብዙ ጊዜ አሳደደው፡፡ ዳዊት ለዚህ ምን ምላሽ እንደሰጠ ዛሬ እንመልከት፡፡ እውነተኛው ታሪክ ከ1ሳሙኤል መጽሐፍ ቀርቧል፡፡

በመሪው መመሪያ ላይ ያሉትን ደረጃዎች በመጠቀም እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን እንዲናገር አድርግ፡፡

የውይይት ጥያቄዎች

1. ዳዊት ለንጉሡ ሳኦል ምን አደረገ? ለምን? ስለዚህ ነገር በኋላ ምን ተሰማው?
2. የዳዊት ሰዎች ዳዊት በንጉሡ ላይ ምን እንዲያደርግ ፈለጉ?
3. ንጉሡን ስለ መጉዳት ዳዊት ለሰዎቹ የተናገረው ምንድነው?
4. ያቆ፡1፡19-20 አንብቡና ተወያዩ፡፡ በዚህ ቦታ፡- ‹‹...ለቁጣም የዘገየ ይሁን፤የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሠራምና›› ይላል፡፡
5. ምሳ፡15፡1 አንብብ፡፡ የለዘበች መልስ ቁጣን ትመልሳለች፤ ሸካራ ቃል ግን ቁጣ ታስነሣለች፡፡ ዳዊት ለዚህ ቃል እንዴት ታዘዘ?
6. አንድ ከሚቆጣ ሰው ጋር ብንሆን ምን ማድረግ አለብን? ይህ ሰው ሲቆጣ ዝም ማለት አለብን? ለዚህ ዓይነት ሰው ምን ዓይነት ምላሽ መስጠት አለብን?
7. ከዚህ ሁሉ ምን ትማራለህ? ሁሉም ቁጣ ክልክል ነው? ስንቆጣ ፈጽሞ ሳንናገር መተው እንችላለን?
8. ቶሎ መቆጣትን መተው እንድንችል እንዲረዳን ከዳዊት ሕይወት የምንማረው ምንድነው?
9. ስትቆጣ ከሚመከተሉ ቃላቶቹ የትኞቹ አንተን እንደሚወክሉ ከቡድንህ አባላት ጋር ተወያይ፡፡
   - በድንገት ቱግ ማለት
   - መጮኽ
   - ማመጽ (ሌላውን መምታት፣ዕቃ መወርወር፣በር መበርገድ)
   - ዝምታ
   - ሌላውን ከመስማት መከራከር
   - ማለት ያልፈለከውን ነገር ብለህ በኋላ መጸጸት
   - ጥርስን ማፏጨትና የአንገት ጡንቻን መወጠር
   - መጥፎ ድምጽ ማሰማት
   - ለቁጣችን ምክንያት አለማቅረብ

- ትዕግስት ማጣት፣መበሳጨት
- በደልን መቁጠርና ማስታወስ

<u>ምሳ፡29፡11 በቃልህ አጥና፡- ሰነፍ ሰው ቁጣውን ሁሉ ያወጣል፤ጠቢብ ግን በውስጡ ያስቀረዋል።</u>

**<u>ትምህርት፡21፡ ቁጣ፡ ዮናስ</u>**

**<u>መግቢያ</u>**፡- ምሳ፡29፡11 የቃል ጥናት ክፍሉን እንደገና ከልስ። እኛ ሁላችንም ቁጣን በተለያዩ መንገዶች እንገልጻለን። አንዳንድ ሰዎች ልክ እንደ ፍንዳታ ከውስጣቸው እስኪወጣ ያቆያሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ አያፈነዱትም፤ ነገር ግን እንደ መርዝ በውስጣቸው ያቆያሉ። እነርሱን ያስቆጣቸው ምን እንደሆነ ያስባሉ። እነዚህ ሰዎች መራራ ቁጣ ያስተናግዳሉ። በዚህ ሳምንት አንድ ሰው ቁጣውን እንዴት እንዳሳየ እንማራለን። ዮናስ እግዚአብሔር ወደ ነነዌ የላከው ነቢይ ነበር። የዚህ ከተማ ሰዎች የዮናስና የአገሩ ጠላቶች ነበሩ። የነነዌ ሰዎች ንስሐ ስለገቡ እግዚአብሔር አላጠፋቸውም። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል።

በመሪው መመሪያ ላይ ያሉትን ደረጃዎች በመጠቀም እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን እንዲናገሩ አድርግ።

**<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>**

1. ዮናስ የተቆጣው ለምንድነው?
2. ቁጣውን እንዴት ነበር የገለጸው?
3. እኛ ቁጣችንን በዚህ መንገድ ስንገልጽ የሚሆነው ምንድነው? ሁል ጊዜ ዝም ማለት ጥሩ ነው?
4. ኤፌ፡4፡31-32 አንብቡና ተወያዩ። ንዴታችንና ቁጣችንን ምን ማድረግ አለብን? ክፋት ምንድነው?
5. ዮናስ እጅግ በጣም ስለተቆጣ ለመሞት ፈለገ። ቁጣን ሳናስወግድ ስንቀር መራርነት ይመጣል። መራርነት ከመርዝ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?
6. ኤፌ፡4፡26 አንብቡ። እኛ ምን እንድናደርግ ነው እግዚአብሔር የሚያዘን?
7. ዘሌዋ፡19፡17-18 አንብቡ። ከዘህ ክፍል ምን እንደምትማሩ ተወያዩ። ይህ ግልጽ ትዕዛዝ ነው።
8. ዘሌዋ፡19፡17 ዝም እንድንል ሳይሆን ለጎረቤቶቻችን እንድንናገር ይነግረናል። እኛ እንዴት መናገር እንደምንችል ያዕቆ፡1፡9 እንዴት ይረዳናል?

**<u>ትምህርት፡22፡ መራርነት</u>**

**<u>መግቢያ</u>**፡ እኛ ልንቆጣ እንችላለን ግን ማንንም አንገድልም። ከአሥርቱ ትዕዛዛት አንዱ አትግደል የሚል ነው። ኢየሱስ አትግደል የሚለውን ብቻ ሳይሆን ከዚያ ያለፈ ነገር

አስተምሮናል፡፡ የኢየሱስ ዋና ትምህርቱ ሕብረት፣ፍቅርና ሰላም ይኑራችሁ የሚል ነው፡፡ የዛሬው ትምህርት ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

ማቴ፡5፡21-26

**<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>**

1. በዚህ ክፍል የሚያስተምረው ማነው?
2. በዚህ ክፍል ኢየሱስ የሚያወግዘው አመለካከትና ስሜት ምንድነው? ኢየሱስ ይህን ለምን እንደሚያወግዝ ከሌሎች ክፍሎች የተማርከው ምንድነው?
3. መጥፎ ቃላቶችን በመጠቀም ቁጣን ስለ መግለጽ ኢየሱስ ምን ይላል?
4. ሰባ አንድ አባላት ያሉት ሸንጎ የሚመራው በሊቀ ካህን ነው፡፡ በሸንጎ ፊት መቅረብ በጣም ከባድ ነገር ነው፡፡ አንድን ሰው ጨርቃም የሚለው የሌላውን መልካም ስም ያጎድፋል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ስድብ የሚሳደበው ሰው ልቡ ምን እንደሆነ ያሳያል? ያንን ሰው የሚገጥመው አደገኛ ሁኔታ ምንድነው?
5. አንድን ሰው አስከፍተን እንደሆነ ኢየሱስ ምን እንድናደርግ ነው ያዘዘን?
6. እግዚአብሔር አምልኳችንን እንዲቀበል ከወንድሞቻችን ጋር ይቅርታ መደራረግ አለብን፡፡ ስለዚህ መሠረታዊ መርህ ተወያዩ፡፡
7. ከአንድ ሰው ዕዳ ቢኖርብን ምን ማድረግ አለብን? (ቁ.25 እና 26)
8. ኤፌ፡4፡31-32 አንብብ፡፡ በዚህ ክፍል የተገለጹት ሁለቱ **<u>ትዕዛዛት</u>** ምንድናቸው?

በኤፌ፡4፡31-32 ያሉ ቃላቶች ትርጉም፡፡ በመራርነት የጀመረው ስሜት ሄዶ ሄዶ አንድ ነገር ላይ እንደሚደርስ ልብ በሉ፡፡

1. **መራርነት**፡- የግሪኩ ትርጉም ይህንን እንደ ስለት ብላዋ የሚቆርጥ ይለዋል፡፡ እንዲሁም ደግሞ መርዛማ ቃና ያለው ነገር እንደሆነ ይገልጸዋል፡፡ ብዙ ነገሮች ሊያቆስሉና መራርነትን ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡
2. **ንዴት**፡- እንደ ቁጣ ያለ ነገር ሆኖ ቶሎ ቱግ ብሎ መናደድ ነው፡፡ ይህ ሁሌ የሚመነጨው ከመራራ ልብ ነው፡፡
3. **ቁጣ**፡- ልክ እንደሚነድ እሳት ይነዳል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ መራርነትንና ንዴትን ያካትታል፡፡
4. **መንጫጫት**፡- በከፍተኛ ድምጽ መጮኽ ነው፡፡ በስሜት ውስጥ ገብቶ መከራከር ነው፡፡
5. **መሳደብ**፡- መተቸት፣ህልናን የሚጎዱ ቃላቶችን መጠቀም፣ሌሎችን ጥፋተኛ አድርጎ መቁጠርና በቃላት ለመበቀል መፈለግ፡፡ ስድብ የመራርነትና ቁጣ ፍሬ ነው፡፡
6. **ክፋት**፡- ጠማማነት፣ሌሎችን ለመጉዳት የሚፈልግ ክፋት፣አብዛኛውን ጊዜ ሌሎችን በመደብደብ የሚገለጽ ነው፡፡

በቁጣ ምክንያት የሚመጡትን ችግሮች እንድናስወግድ እግዚአብሔር ከእኛ ይፈልጋል፡፡ እግዚአብሔርን እንድንታዘዝ የሚረዱ ነገሮች ከዚህ በታች ቀርበዋልና ተወያዩ፡፡

- ከመናገርህ ወይም አንድ እርምጃ ከመውሰድህ በፊት አስብ፡፡
- ሁል ጊዜ ከሚቆጣ ሰው ጋር የቅርብ ጓደኛ አትሁን፡፡

ምሳ፡22፡24-25፡- ከቁጡ ሰው ጋር ባልንጀራ አትሁን፤ከወፈፍተኛም ጋር አትሂድ።

- ረጋ በል፡- ሌላውን ለመጉዳት፣ለመበቀል፣ ለማስቆጣት ብለህ አትናገር። ተረጋግተህ ጠቃሚ ቃላቶችን ተጠቀም። ሌላው ቁጣውን መቆጣጠር ቢያቅተው አንተ ቁጣህን መቆጣጠር እንደምትችል ጥሩ ቃላቶችን በመጠቀም አሳየው። ረጋ ማለት ፈጽሞ ቁጣን በሚገልጽ ከፍተኛ ድምጽ አንናገርም ማለት አይደለም።
- እንድትቆጣ ያደረገህን ችግር ለማቃለል ሞክር። ይህ ግልጽ ይመስላል፤ነገር ግን አብዛኛው ሰው ተቃራኒውን ያደርጋል። ያስቆጣንን ችግር ለማቃለል እየሠራን ነን ማለት እንችላለን፤ ነገር ግን በእውነቱ ያስቆጣንን ሰው ለመጉዳት እንሞክራለን። ችግሩን ከማጥቃት ፋንታ ሰውዬውን እናጠቃለን።
- **ችግሩን ለማቃለል ሄደህ ችግሩን ከፈጠረው ሰው ጋር ተነጋገር።**

ማቴ፡5፡22-24 (ሉቃ፡17፡3-4) ለመታረቅ መነጋገር እንደሚያስፈልግ ይናገራል። (ማቴ፡18፡15-17)

- ሌሎች የሚሉትን ለመስማት ፍቃደኛ ሁን። ያቆ፡1፡19፡- ስለዚህ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ለቁጣም የዘገየ ይሁን። የሚቆጡ ሰዎች ለሌሎች ዕድል አይሰጡም። ለራሳቸው ብቻ ለመናገር ይፈልጋሉ። ይህ ተገቢ አይደለም፤ለችግሩም መፍተሔ አይሆንም። ለሌሎች ጊዜ ሰጥተን ልንሰማቸው ይገባል።
  ማቴ፡7፡3-5፡- በወንድምህም ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለምን ታያለህ፤በዓይንህ ግን ያለውን ምሰሶ ስለምን አትመለከትም። ከሌሎች ጋር ስንነጋገር እኛም ጥፋተኞች ልንሆን ስለምንችል ማረጋገጫዎችን በትክክል መፈለግ አለብን።
- የጉዳችኋቸውን ሰዎች ይቅርታ ልትጠይቋቸው ይገባል። ሉቃ፡17፡3-4፡- ወንድምህ ቢበድልህ ገስጸው፤ቢጸጸትም ይቅር በለው። በቀንም ሰባት ጊዜ እንኳ ቢበድልህ በቀንም ሰባት ጊዜ፡- ተጸጸትሁ እያለ ወደ አንተ ቢመለስ ይቅር በለው። እንዲህ ዓይነት ነገር ማድረግ የሚያስፈልገው ሰው ይህን ነገር ቢያደርግ ብዙ ቤተሰቦች ይታረቁ ነበር፤ብዙ የቤተክርስቲያን መሪዎች ይታረቁ ነበር፤ብዙ ወዳጆችና ጎሬቤቶችም ይታረቁ ነበር።
- **ራስ ወዳድነትን ቁጣ** ካለ አስወግድ። ባታስወግድ እንደ ቁስል አመርቅዞ ችግር ይፈጥራል።
- ይቅርታን ወደ ማድረግ ሕይወት ፈጥነህ ተመለስ። ሩህሩህና ልበ ሰፊ ሁን።

## <u>ትምህርት፡23፡ ስግብግብነት</u>

መግቢያውን አንብብ። ዓለም ብዙ ነገሮችን ታሳየናለች። አለም የምንፈልገውን ሁሉ እንምናገኝ ታባብለናለች። ሥጋ ካለ ‹‹ብሉ፤ብሉ፤ብሉ›› ትለናለች። ነገር ግን መጽሐፍ እንደሚለው ከሆነ ብዙ መብላትና ብዙ መጠጣት በልባችን ውስጥ ችግር እንዳለ በግልጽ ያሳየናል። በምሳ፡23፡20 ላይ ይህ ስግብግብነት እንደሆነ ተገልጧል። ኤሳው የይስሐቅ ታላቅ

ልጁ ነበር። አደን ማደንና ጥሩ ነገር መብላት ይወድ ነበር። የኤሳውን ልብ የሚያሳይ ታሪክ ከዘፍጥረት ቀርቧል።

በመሪው መመሪያ ላይ ያሉትን ደረጃዎች በመጠቀም እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን እንዲናገር አድርግ።

**<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>**

1. ስለ ኤሳው ምን ትማራለህ?
2. ከእግዚአብሔር በረከት ይልቅ ኤሳው የበለጠ ዋጋ የሚሰጠው ለምን ነበር?
3. ዕብ፡12፡17-18 አንብብ። ከዚህ ክፍል ጋር አያይዘህ ስለ ኤሳው ምን ትማራለህ? የታላቅ ልጁ በኩርነት እግዚአብሔር ለአብርሃም ምድርንና በረከትን እሰጣለሁ ብሎ የገባውንም ተስፋ ቃል ያካትታል።
4. መናቅ ማለት አንድን ነገር ዋጋ እንደሌለው መቁጠር ወይም ዝቅ አድርጎ መመልከት ነው። ኤሳው የናቀው ምን ነበር?
5. የስግብግብነት ትርጉም ምንድነው?
6. ፍልጵ፡3፡19 አንብብ። ስለ ስግብግብነት የእግዚአብሔር ሀሳብ ምንድነው? ለምን?
7. የእኛ እርካታችን ማነው? ለምኞት ማንን መፈለግ አለብን?
8. ምሳ፡23፡19-21 አንብብ። በዚህ ክፍል እግዚአብሔር የሰጠን ትዕዛዝ ምንድነው? በቁ.21 መሠረት የስግብግብነት ውጤት ምንድነው?
9. እኛ ስግብግቦች ላለመሆን ራሳችንን መግዛት እንዴት ማዳበር እንችላለን? ገላ፡5፡22 እና 1ጢሞ፡4፡4-5

**<u>ማጠቃለያ፦</u>** ለምግብ መስገብገብ የሰውነትን ክብደት ስለሚጨምር በጤና ላይ ጉዳትን ያመጣል። የልብ ድካም፣የጉልበት ላይ ችግርና የጀርባ ሕመም ሊያስከትል ይችላል። አልኮልን መጠጣት ከሌሎች ጋር ያለውን ግንኙነት፣አእምሮንና የውሳኔ ሰጪነትን ችሎታ ይጎዳል። <u>ነገር ግን እዚህ ጋ ሊሰመርበት የሚገባው ጤናማ አመጋገብና ጤናማ ነገርን መጠጣት ሐጢአት ነው ማለት አይደለም።</u> እግዚአብሔር ጥሩ ምግብና መጠት ሰጥቶናል። ይሁን እንጂ ከመጠን በላይ መብላት ሐጢአት ነው። ስለዚህ የራሳችንን ምኞት ብቻ መፈለግ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ከማበላሸቱም ባሻገር በሕያው ፍቅሩ እኛን ሊያጠግበን ከሚፈልገው አምላክ ይለየናል። ራስህን እንዲህ ብለህ ጠይቅ፦‹‹ከሁሉም ነገር በላይ ምንን መፈለግ አለብኝ?››

## <u>ትምህርት-24፡ ስንፍና</u>

**<u>መግቢያውን አንብብ</u>**። የስንፍና ትርጉሙ አንድን ነገር ለመሥራት ቀልጣፋ አለመሆን፤ወይም ለመሥራት አለመፈለግ ነው። የምሳሌ መጽሐፍ የዚህ ዓይነት መሥራት የማይፈልገውን ሰው ሰነፍ ይለዋል። ዛሬ ስለ ሥራ በመጽሐፈ ምሳሌ እግዚአብሔር የሚሰጠውን ትዕዛዝ ተማር። ስለ ሥራ ያለህን አመለካከትና ልምድ ወደ ኋላ መለስ ብለህ አስብ።

1. ስለ ሃኬተኛ (ሰነፍ) ባሪያ ታሪክ ከማቴ፡25 መለስ ብለህ ተመልከት፡፡
2. ሰነፍ ሰው ለስንፍናው ምክንያት የሚያደርገው ምንድነው? ከሰነፍ ሰው ሕይውት የሚመነጨው ምንድነው? ምሳ፡24፡3034 አንብብ፡፡
3. የሰነፍ ሰው ችግሮች ምንድናቸው? ምሳ፡6፡9 እና 26፡4
4. ሰነፍ ሰው ለስንፍናው የሚሰጠው ምክንያት ምንድነው? ምሳ፡22፡3 እና 26፡16
5. የሰነፍ ሰው ሕይወት አጥፊ የሚሆነው እንዴት ነው? ምሳ፡18፡9
6. ስለ ሰነፍ ሠራተኛ ቀጣሪዎቹ ምን ይሰማቸዋል? ምሳ፡10፡26
7. እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ምን እንድናደርግ ነው? ቆላ፡3፡23
8. እግዚአብሔር ለአብያተክርስቲያናት የሚሰጠው ትዕዛዝ ምንድነው? 2ተሰ፡3፡10
9. አንድ ሠራተኛ ጥሩ ሥራ እንዲሠራ ሊያነሳሳ የሚችለው ምንድነው? ምሳ፡16፡26
10. ሰነፍ ሠራተኛን ከታታሪ ሠራተኛ ጋር አነጻጽር፡፡ ምሳ፡10፡4, ምሳ፡12፡24, ምሳ፡14፡23 እና ምሳ፡28፡19
11. ብዙ ሰዓት ስለ መሥራት ጠቢቡ ሰሎሞን ምን ይላል? ምሳ፡23፡4-5
12. ለአንድ ነገር ቅድሚያ ለመስጠት እንዲረዳን ከምሳሌ መጽሐፍ መማር የምንችለው ምንድነው? ምሳ፡15፡16, ምሳ፡15፡17, ምሳ፡17፡1 እና ምሳ፡28፡6
13. በሥራ ላይ ስላለህ አመለካከትና ልምድ ዛሬ የተማርከው ምንድነው?

## ትምህርት-25፡ ስርቆት

መግቢያውን አንብብ፡፡ ስርቆት(ሌብነት) በዓለማችን ላይ አለ፡፡ ሰዎች የሰውን ቤት ሰብረው ይገቡና የሰውን ንብረት ይሰርቃሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ከመሥሪያ ቤት ይሰርቃሉ፡፡ የዛሬው ታሪክ ስለ ስርቆት የእግዚአብሔር ሀሳብ ምን እንደሆነ ያስተምረናል፡፡ ይህንን ታሪክ ስትሰማ የራስህን ሕይወት ፈትሽ፡፡ የእሥራኤል ሕዝብ በእያሪኮ ላይ ታላቅ ድልን ተቀዳጅተው ወደ ተስፋይቱ ምድር ገቡ፡፡ የእያሪኮ ከተማና በውስጧ ያለው ነገር ሁሉ በቁጥጥር ሥር እንዳለ እግዚአብሔር ነገራቸው፡፡ ይህም ማለት በከተማው ውስጥ ያለው ሁሉ የእግዚአብሔር ነው ማለት ነው፡፡ በኢያሱ፡6፡18-19፡- ‹‹እናንተ ግን እርም ካደረጋችሁት በኋላ እርም ከሆነው ነገር ራሳችሁን ጠብቁ እርም ከሆነው አንዳች የወሰዳችሁ እንደ ሆነ የእሥራኤልን ሰፈር የተረገመ ታደርጉታላችሁ፤ ታስጨንቁትማላችሁ፡፡ ነገር ግን ብርና ወርቅ ሁሉ የናስና የብረትም ዕቃ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ይሁን ወደ እግዚአብሔርም ግምጃ ቤት ይግባ፡፡›› ስለዚህ ከተማውን በሙሉ በእሳት ካቃጠሉ በኋላ ብር፣ወርቅ፣ናስና የብረትም ዕቃ ወደ እግዚአብሔር ግምጃ ቤት ይገባሉ፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉም አይደሉም እግዚአብሔርን የታዘዙት፡፡ ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል ቀርቧል፡፡

በመሪው መመሪያ ላይ ያሉትን ደረጃዎች በመጠቀም እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን እንዲናገር አድርግ፡፡

### የውይይት ጥያቄዎች

1. አካን ያደረገው ምን ነበር?
2. ለዚህ እግዚአብሔር የሰጠው ምላሽ ምን ነበር?
3. አካን ይሰርቅ የነበረው ከማነው?

4. የእሥራኤል ሕዝብ ትንሽዋን ከተማ ጋይን ሲወርሩ የተከሰተው ነገር ምንድነው?
5. የአካን ሐጢአት ማህበረሰቡን በሙሉ የጎዳው እንዴት ነበር?
6. እግዚአብሔር ለአካን የሰጠው ቅጣት ምን ነበር?
7. አካን ስለሐጢአቱ የገለጸው እንዴት ነበር? መመኘት ማለት ምን ማለት ነው?
8. መዝ፡(24)፡1 አንብብ። በዓለማችን ላይ ስላለው ሁሉ ነገር የምንማረው ምንድነው?
9. ከሌላ ሰው የጠፋውን ንብረት ብታገኝ ምን ማድረግ አለብህ?
10. ዘኬዎስ የቀረጥ ሰብሳቢ ሲሆን ከሚገባው በላይ ቀረጥ ይሰበስብ ነበር:: በሉቃ፡19፡8 ላይ ዘኬዎስ ያደረገው ምን ነበር? መስረቅ ትክክል አይደለም። የራሳችን ያልሆነ ነገር ብንወስድ ምን ማድረግ አለብን?
11. እግዚአብሔር ሕዝቡና የሕዝቡ የሆነው ንብረት የሚከበርበትን ማሕበረሰብ ይፈልጋል። የሕዝብ ንብረት እንዳይከበር ለማድረግ ሰዎች የሚያደርጉትን ነገር ተወያዩ። ለምሳሌ፡- በትምህርት ቤት ጠረጴዛ ላይ መጻፍ። ይህ እንዴት መስረቅ ሊሆን ይችላል?
12. አንዳንድ ሰዎች ሳይሠሩ ከቀጣሪዎቻቸው ደመዎዝ በመውሰድ ይሰርቃሉ። ይህ መስረቅ ነው ብለህ ታስባለህ? ተወያዩ።
13. እግዚአብሔር ዛሬ ለአንተ የሚለው ምንድነው?

## <u>ትምህርት-26፡ ክለሳ</u>

***<u>መግቢያውን አንብብ</u>***። ከእግዚአብሔር ጋር በቅርበት እንዳንገዝ የሚያደርጉትን ብዙ ሐጢአቶችን አይተናል። ከእነዚህ ሐጢአቶች ጥቂቶቹ ሙት ሐጢአቶች ይባላሉ፤ምክንያቱም መንፈሳዊ ሞትን ያስከትላሉ። በመዝ፡(90) ላይ ሙሴ ሕይወት አጭር እንደሆነች እንድናስብ ነግሮናል። ይህ አጭር ሕይወታችን በከንቱ ሊጠፋ ወይም እግዚአብሔርን ለማወቅ በመፈለግ ሊያልቅ ይችላል። እግዚአብሔር ሐጢአትን እንደሚጸየፍ ሙሴ ነግሮናል። እኛ ቸል ብለን የምንሰራው ሐጢአት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን መንፈሳዊ እድገት ሊያቀጭጭ ይችላል። ሙሴ ሲጸልይ፡- ‹‹የዘመኖቻችንን ዕድሜ መቁጠር እንድንችልና በጥበብ ወደ አንተ መቅረብ እንድንችል አስተምረን›› ብሏል።

- የጽድቅ ሂደት እንዴት እንደሆነ የተማርከውን ከልስ።
- በጽድቅ ሂደት ውስጥ አንተ የቱ ጋ ነህ? ሕፃን? ጎልማሳ? ወይስ አዋቂ?
- ዛሬ አንተን የሚያስቸግርህ ምን ዓይነት ሐጢአት ነው?
- ይህንን ሐጢአት እንድታሸንፍ ሊረዳህ የሚችለው ማነው?
- ለተወሰነ ደቂቃ አንዳችሁ ለአንዳችሁ በመፀለይ ጊዜ ውሰዱ።